# ጥቅምት እና ጥቅምት ሰኔና ሰኞ በህዝብ የተመረጠ መሪና በመድረክ ጭብጨባ የሚሻር መሪ

ሣተናው ቀበሮ

ከዲስ አበባ

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ የተከበራችሁ አድማጮች ሰሞኑን እንደኔው ስትሰሙት በሰነበታችሁት ጉዳይ ውስጤ አዝኖዋል አዘንኩና ዝም አላልኩም ጥቂት እንባ አውጥቼ አለቀስኩ ትንሽ እፎይ ለማለት ያህል እና ዛሬ ደግሞ ከእናንተ ጋር ለመቆየት ወድጃለሁና ብቅ ብያለሁ

ዛሬ ያለንበት ወር ጥቅምት ነው ከወሩም ቀኑ ግፍ የተዋለባቸው ወገኖች በጥይት በአደባባይ የተገደሉበት እለት ነው ማን ነበር የገደላቸው? ታሪክ ነው የሚያውቀው ግን ሞተዋል የብዙዎች ቤት በሃዘን ተዘግቶዋል ቀባሪ ጉድ እይ ያለው ቤተሰብ ማቅ ለብሶ አንጀቱ በሃዘን

አርሮ ኩርምት ያለው በዚህ በጥቅምት ወር ነበር በምርጫው ማግስት በመጣው ጥቅምት ወር

እናም ይህን ጽሁፍ የሚያነበው የሬዲዮ አዘጋጅ ለሰከንዶች ትናፋሹን ውጦ ዝም ይበል፤አድማጭም ለሰከንዶች ግዜ የሰጣቸው ገዳይ ባለጥይቶች ተኩሰው እንደወጣ የሚያስቀሩት ወገን ሞት ፤እግዜር ይማርህ ለመባል ያልታደለ አሙዋሙዋት ፤

የሚጸጽት መሆኑን ያስብ ዘንድ ይሁን //////

እግዚያብሄር ይስጣችሁ፤ ቦርቆ ያልጨረሰውን ልጃችሁን አይደለም፤ የምትጦሩትን ወላጅ አይደለም፤ እህትና ወንድም አይደለም ፤የምታውቁት ወገናችሁን አይደለም ፤የባእዳን አገር ነዋሪም እንዲህ ያለ ሞት ሃዘኑ ከውስጥ አይወጣ ልብም በቶሎ አይጠገን እና እንዲህ ካለው ይሰውራችሁ ጠዋት ግንባሩን ስማችሁ የላካችሁት ልጅ ተገደለን ስትሰሙ .. ዋ.. የወላድ አንጀት ይፍረዳ.. .. ሌላማ ምን ይባላል?

በጥቅምት አንድ አጥንት ይትበሃል ውሉ ከብርድ ለመጠበቅ አጋዥ ስለማግኘት የተነገረ ነበር እንጂ የአጥንትን ክፋይ የቤተሰብን አባል በአደባባይ በጥይት

እያስገደሉ ዝም የሚባልበት ወር አልነበረም ምን ያደርጋል ሆነ

እንግዲህ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ የሚፈልገውን መረጠ የመረጣቸው አቅም ይኑራቸው አይኑራቸው ገዳይ ይሁኑ አይሁኑ ከምርጫው በሁዋላ ወያኔ እንዳራገበው ሳይሆን ዋናው ቁም ነገሩ ህዝብ የወደደውንና ያመነበትን የመምረጥ መብት አለው ወያኔ የሚለው ነበር

በሚገባ ተመለሰ ህዘብ ያመነባቸውን መረጠ በብርሃን ፍጥነት የህዝብ ድምጽ ተነጠቀ አይሆንም አልሰረቅም አለ ሌባን የተከላከለ አልሰረቅም ያለ ህዝብ በአደባባይ እንዲገደል ሆነ

ግንቦት ሰባት ምርጫው ተደረገ ግንቦት ሰባት ማታውኑ ቁንጮው መለስ ዜናዊ የመሰብሰብና የመሰለፍን መብት በመግፈፍ አይቻልም አሉ ጭራሽ የፌዴራል ፖሊስና የመከላከያውን ሃይል ደርበው በእሳቸው እዝ ስር እንዲውሉ ማድረጋቸውን በመነጽራቸው መስታወት እያሾለቁ በመዛበት ነገሩን

ግንቦት 28 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በወያኔ ደህንቶች ሲደበደቡ ሲጮሁ አደሩ ግንቦት 29 ከድብደባ ያመለጠው ተማሪ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄ አነሳ

አንደኛ የተሰረቀውን የወገኔ ድምጽ ይመለስልን ሁለተኛ በጉዋደኞቼ ላይ የተደረገው የድብደባ እርምጃ

እንዳይደገም ተደብድበው ታፍነው የተወሰዱትም ይመለሱ አለ የሚሰማው አጣ ቁጣው ተቀጣጠለ ወያኔ በእሳቱ ላይ ቤንዚን አርከፈከፈ

ኦራል የተባሉትን ወታደራዊ ካሚዎኖች ዩኒቨርስቲው ድረስ አስገብቶ ተማሪዎችን አፈሰ ወደ ሰንዳፋ ፖሊስ ማሰልጠኛ ሊወስድና አስሮ ሊደበድባቸው ቁዋምጦ ኮተቤ ላይ ሲደርስ ወገን ተባበረ ድንጋይ ሳይወረውር መንገድ ዘግቶ ወገኖቼን ልጆቼን ወዴት ? አለና አላሳልፍ አለ

የወያኔ ቅልብ ወታደር ግን መተኮስ ጀመረ ጥይት ይተፋ ጀመር ወገን በወገኑ የግድያ እርምጃ ወሰደ የወያኔን ከሌሎችም የአፍሪካ አምባገነን መንግስታት የግድያ እርምጃ ለየት የሚያደርገው ወገን ጥቃት የሌለበት ሰላማዊ ተቃውሞ በሚያሰማ  ወገኑ ላይ ተኩሶ ግዳይ መጣሉ ጀብደኛ መባሉ ነው

ከቀናት በፊት ቁንጮው መለስ ዜናዊ ወታደሩንም ፖሊሱንም የማዝዘው እኔ ነኝ ብለው ስለ አዛዥነታቸው እቅጩን በነገሩን ሰሞን ቅልብ ወታደሮቻቸው ታዘዙ ግደሉ ተባሉ የመጀመሪያ ግዳያቸውንም ኮተቤ ላይ አንድ አሉ አፈሙዛቸውን በንጹሃን ደም አሙዋሹ ሽብሬ የተባለችውን ወጣት በልጅነትዋ ቀጩና ጣሉዋት  ከዚህ በሁዋላ ሰኔ አንድ አዲስ አበባ በንጹሃን ሰዎች ደም ጎርፍ ተጥለቀለቀች

ቁንጮው ሰውዬ ከአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ሲያዙ የወያኔ ወታደር ቃታ ይስባል ሆስፒታሎች ተጨናነቁ አስከሬን በአስከሬን ላይ ተደረበ ወያኔ ግን  ለመግደል ብዬ ደክሜያለሁና የድካም ዋጋዬ ይከፈለኝ አለና ለአስከሬን ዋጋ ጠየቀ ደፋር ገዳይ አይደለም ጎበዝ ?

ሰኔም አለፈ ሃምሌ ነሃሴ መስከረም አለና ጥቅምት መጣ ያው ነው እንደቀጠለ ነው ግድያው አፈናው እስራቱ መሰወሩ ቤት ለቤት ሰብሮ መግባቱ ሁሉም እየሆነ ነበር የዘለቀው

እኔም ጥያቄዬ የሚነሳው ከዚህ ነው የዚያን ግዜ ያ ሁሉ የተከፈለ መስዋእትነት ለማን ነበር? የፈለግኩትን መረጥኩ ድምጼ አይሰረቅም አለና ነው እንጂ ሌላ ምን ጥቅም ነበረው? ድምጽ የሰጠውና አልሰረቅም ያለበቱ መሪው ማን ነበር ? እስከሚገባኝ ለቅንጅት ሲል ህዝብ የከፈለው መስዋእትነት ነው

ታዲያንን ምነዋ ? ዛሬ የጆሮዋችን ታምቡር እስከሚበጠስ ወያኔ እና አጨብጫቢዎቹ በሳቅ ፍርስ እስከሚሉ ድረስ መሳቂያ አጀንዳ መስጠታችሁ ምነዋ ? የዚያን ግዜ የተከፈለው የነብስ ዋጋ ቢዘነጋ እንኩዋን በዚሁ በጥቅምት ወር የቅንጅት መሪዎች ታሰሩ ሲባል ወይኔ መርጬ አሳሰርኩዋችሁ ብሎ ደረት የደቃ ፤ጸጉር የነጨ ፤እንዳበደ ብቻውን መነጋገር የጀመረ ወገን ነበራችሁ

ቤተስኪያን በባዶ እግሩ እየተመላለሰ መስጊድ ሶላቱን ሳያቋዋርጥ ፈጣሪውን ሲማጸን የነበረ ወገን ነበራችሁ በእናንተ ጉዳይ ሲነጋገርም ሆነ ሲያስብ እንባው ቀድሞ የሚያለቅስ ወገን ነበራችሁ

ታምሞ በተኛበት እንኩዋን ምነው እንዲህ አመመኝ? የእነዚህን ሰዎች መጨረሻ ሳላይ እንዳልሞት ብሎ ፈጣሪውን የሚሞግት ወገን ነበራችሁ

በዚህ ወገን በዚህ ህዝብ ጸሎትና እንባ እንጂ ተጠየቀ በተባለው ምህረትም ሆነ በአሜሪካ በጎ ፈቃድ ወይንም በወያኔ ይቅር ባይነት ከወህኒ እግረ ሙቅ እንዳልተለቀቃችሁ ልታውቁት ይገባል በእርግጥ ዛሬም በሆነው ሁሉ እንዲያለቅስ እንባው እንዲፈስ አደረጋችሁት

ይህ ህዝብ ስንት ግዜ ማልቀስና ማንባት አለበት ከትናንት በስትያ በኢህአዴግ እኩይ የግፍ ድርጊት ሲበዛበት አለቀሰ እናንተን መረጠና ድምጹ ሲነጠቅ አላስነጥቅም በማለቱ ተገደለ ተገረፈና አለቀሰ ስትታሰሩበት መሪዎቼ ታሰሩ ብሎ አለቀሰ  ወደ ፋጣሪው አንጋጦ እና አጎንብሶ እያለቀሰ ተማለደ ስትፈቱ ከእንግዲህ እንባ በቃኝ ብሎ ነበር ግን አልሆነም ዛሬም በሆነውና በሚሰማው ሁሉ ያለቅሳል ግን ለምን ያልቅስ ?አያሳዝናችሁም ? የቱን ነው ታዲያ ለአንተ ነው የምትሉት ?

በነገራችን ላይ የመነታረኪያው ግዜ አሁን ነበር ብዬ አላምንም ቀድሞውኑ ለጉዞ ሲታሰብ ያላማረበት ጉዳይ ነበርና እዚያ ውስጥ ገብቼ መናገር አልፈልግም ግን አስር ግዜ እያነሳችሁ የምትጥሉት ከአፋችሁ በማይነጠለው ህዝብ ለሚለው ስም ትንሽ አሰብ አድርጉ እና እዘኑለት

እነማን ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ ከእኔ ይበልጥ ራሳችሁ ራሳችሁን ታውቁት የለም እንዴ ? ይህን በስሙ የምትምሉለት ህዝብ ሁለት ነገር አሳይቶዋችሁዋል አንደኛው ምንም ቢሆን ማልቀስ እንጂ ምንም አያደርግምን ጠንቅቃችሁ ታውቃላችሁ አዎን ያለቅሳል እንባው ግን ለመአት ከሆነ መአት ያመጣል ለምህረት ከሆነም የፈጣሪን አንጀት ያራራል

ሌላው ሁለተኛው ነገር ታዝቦ ያልፋል እንጂ ምን አያመጣም ይሉት አባዜ ከጉዋደኞቻችሁም ቢሆን እየወረሳችሁ ነው የኢህአዴግን ችለን ዝም ማለታችን ታዝበን አለመናገራችን ቀደም ሲል የወረሰን የፍርሃት እከክ እያሳከከን ነው ከእናንተ በግንቦት ወር መምጣት ጋር ተከትሎ ያ የፍርሃት እከክ ረግፎልናል ከዚያ ወዲህ እምቢ ማለት ችለናል በእርግጥ አንድ ጉዳይ ታዝበን አልፈናል ለዚህ ለእናንተ ትርምስ የጠዋቱ ተጠያቂ ልደቱ አያሌው ሳንኮረኩመው ዝም ብለነዋል ሳይነግስ የሞተው ንጉስ ብለን አሳንሰን ለማየት ሞከርንና ተውነው ይህን

በማወቃችሁ ኢህአዴግን የመሰለ ግፈኛ ስርአት ዝም ያለ ህዝብ ፤ልደቱን የመሰለ ከሃዲ ዝም ያለ ህዝብ፤ በሚያምንብንና በሚወደን በእኛ ላይ ምን ሊያደርግ ይችላል ? የሚል ስሌት የሚከተሉ ሰዎች አሉ ያለውን ባልንጀሬን ሃሳብ ልጋራው ተገድጃለሁ

አይምሰላችሁ በእርግጥ ከላይ የተባለው እውነት ነው ግን ከእንግዲህ ይህ ህዝብ ዝም የሚል አይምሰላችሁ ለሆነው ሁሉ ተጠያቂም አድርጎ ይከሰናል ብላችሁ አትስጉ በአገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ መሃይሙንም አየው የተማረውንም አየው ከዚህ የተሻለ ከቶም የለምና ከአክብሮት በወረደ የጥላቻ ስሜት ውስጥ ተዘፍቆ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል አትጠራጠሩ እመኑኝ በሆነው ሁሉ የተጎዳው ምን ይል መሰላችሁ ? እንዲህ የሆንኩት ለመሬት ብዬ አይደለም ለነጻነት ብዬ ነው ነጻነቴን ለድርድር የሚያቀርበውን ደግሞ እንደጉዳቴ መጠን አስከፍለዋለሁ እያለ ነው ይህ አባባሉ ማንንም ሆነ ማንንም የሚመለከት ነው መታለል ዘለላለም እንታገልልሃለን ብለው እየመጡ መልሰው እሱኑ በሚታገሉ ሃይሎች አስመሳይነትና አታላይነት ከመኖር ለታወቀው ግፈኛም ሎሌ መሆን ሞት ነውና ሞት ደግሞ አይቀሬ ከሆነ አንድ ይዞ መሞት ክብር ነው እስከማለት ደርሶዋል

መቼም በእርጋታ ላየው ልዩነት በሉት ዲሞክራሲያዊነት ፈረንጅ ጆሮ ካልደረሰ በሬዲዮ ካልተራገበ ስምምነት አይመጣም እንዴ? ይህን መቻል ያልቻለ መሪ የህዝብን ጥቅም ለማስከበር በሚደረገው ትግል ምኑን ይችለዋል?

ወግና ደንቡን፤ ህግና ስርአቱን መከተል ያልወደደ ህዝብን ይወድድ ይሆን እንዴ? ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ሆነና የህዝብ መንፈስ ነው ያልነውን ቅንጅት መሪ ለመናቅና ለመሳደብ የሞከረ ለማንጉዋጠጥ አፉን ያሾለ ነገ እኔንና ወገኔን ላይሞልጨን ምን ዋስትና አለን ?

በተለይ እናንተው እዚያው ፈረንጅ አገር ለኖራችሁ «ማንነትህን እንድነግርህ ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝ» ይላል ፈረንጅ ትሉን የለም እንዴ?

ታዲያንን ከማን ጋርስ ነው የምትውሉት ? ትናንት እናንተ በእስር ቤት ስቃያችሁን ስታዩ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ቤት ሆነው አዘዙ እያለና እያስባለ በምናቡ የፈጠረውን ድርጅት ህልው አድርጎ በአዲስ አበባ ተማሪዎችን ሲያስገድል የኖረው ስም አይጠሬ እና መሰሎቹ ናቸው እኮ የእናንተን ጉዳይ እያራገቡ ያሉት

እነዚህ ሰዎች እኮ በዚህ ጉዳይ በግላቸው በለጸጉ፤ ከአሜሪካ አዲስ አበባ ድረስ ተሻግሮ በነጻው ጋዜጣ ስም የሚንቀሳቀሱ ሁሉ እየከበሩ ነው አራግቡልን እሳቱ

እንዳይጠፋ ቆስቁቁሱልን እየተባሉ ገንዘብ እየሰበሰቡ ነው ይህን እንኩዋን አታውቁም

እነዚህ ሰዎች በታሰሩበት ለምን ያላደረጉትን እንዳደረጉ ሆኖ ይቀርባል የሚባለው ድርጅት አገር ቤት የለም ምነው? ብለው ጠይቀው የነበሩ ወዳጆቼ ሞት ነው የሚፈረድባቸው እነሱ አይወጡ እያለ እጣ ሲጣጣልባችሁ የነበረ ሞታችሁን ለመስማት ጆሮውን ሲኮረኩር የነበረ ግለሰብ የዚያን ግዜ ባመጣው ጦስ በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በወያኔ ጥይት ተገድለው ሬሳቸው ሳምንት አልፎ የተገኙ ተማሪዎች ነበሩ

ይህን ያደረገ ግለሰብ ጋር ተለጥፎ ዛሬም ይህን እንዲያራግብ መፍቀድ ወይንም አይቶ ዝም ማለት ምን ማለት ነው? የዚያን ግዜ መስዋእትነቱን የከፈሉት አለፉ እናንተም ያመንንባችሁ ለዚህ በቃችሁ

ሙዋቾቹ ግን ቀን ጎደለባቸው ሰኔና ሰኞ ገጠመባቸው ብለን ዝም የምንል ከእንግዲህ የምንኖር ይመስላችሁዋል? እንጃ ሰኔና ሰኞ ስለገጠመ ሞተ ብለን ታጋይ አልባ የምንሆን የረከስን ትውልዶች እንዳልሆንን ይገባኛል

ወደ መነሻዬ ልመልሳችሁና ላብቃ በመጠኑም ቢሆን የማዝነው የሰላምና የዴሞክራሲ ሰማእታትን በምንዘክርበት ጥቅምት ወር ላይ ሆነን በጥቅምት ወር ሌላ ጉድ

መስማታችን ነው በጥቅምት ወር ያጣናቸውን ዘከርን ፤ በጥቅምት ወር በህዝብ የተመረጠ መሪ በመድረክ ጭብጨባ ይውረድልን አልን ፤አዬ ጥቅምት ስንት ጉድ አሳየን ? በዚህ ላይ የምትጨምሩት ቢኖር ጨምሩ እኔ ግን አበቃሁ

ሳተናው ቀበሮ

ከአዲስ አበባ